የተጨባጭ እውነታ ሰነድ

SAFE HOMES FAMILIES COMMUNITIES

# ዓመፅን ለሚጠቀሙ ሰዎች እገዛ እና ድጋፍ

*አውስትራሊያ ውስጥ የቤተሰብ እና የጾታ ጥቃት በምንም ዓይነት ሁኔታ ተቀባይነት የለውም። በቤት ውስጥ ቢከሰቱም የቤተሰብ ጥቃት እና የጾታ ጥቃት ወንጀሎች ናቸው።*

አውስትራሊያ ውስጥ ቢወለዱም ወይም ከሌላ ሀገር ወደ አውስትራሊያ ቢዛወሩም ማንኛውም ሰው ከፍርሃትና ከዓመጽ ነፃ ሆኖ የመኖር መብት አለው።

የአውስትራሊያ ሕግ ሴቶችን እና ወንዶችን በእኩልነት ይመለከታል። እያንዳንዱ ሰው አዎንታዊ እና ደህንነቱ የጠበቁ ግንኙነቶችን የማካሄድ መብት አለው።

## የቤተሰብ ጥቃት

በቤተሰብ የሚፈጸም ጥቃት ወንጀል ነው። አንድ ባል ወይም አጋር በሚስቱ ወይም በአጋሩ ላይ ጥቃት ማድረስ (ጠበኛ መሆን) በሕግ የተከለከለ ነው።

በቤተሰብ ውስጥ የሚፈጸሙ ዓመጾች እንደ ጥቃት፣ ወሲባዊ ጥቃት፣ ዛቻ፣ ማስገደድ፣ ማስፈራራት፣ የቃል ስድብ፣ ጠለፋ፣ ተከታትሎ ማስጨነቅ (ማጥመድ) ወይም ከእነዚህ ነገሮች መካከል አንዱን ለማድረግ መሞከርን የመሳሰሉ ጠበኛ ባህሪያትን ያጠቃልላል።

በቤተሰብ ላይ የሚፈጸም ዓመፅ ከአካላዊ ጥቃት በላይ ሲሆን ኢኮኖሚያዊ በደል፣ ስሜታዊ ጥቃት፣ የቤተሰብ ዓመፅ ትዕዛዞችን መጣስ እና የንብረት ውድመትንም ያጠቃልላል።

በቤተሰብ ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ:

- በአውስትራሊያ ውስጥ የመቆየት መብታቸውን በተመለከተ ማስፈራራትን ጨምሮ ሚስትዎን ወይም የትዳር ጓደኛዎን ማስፈራራት
- በጉልበት መያዝ፣ መምታት፣ ማፈን፣ በእርግጫ ወይም በቡጢ መምታት
- በእነርሱ ላይ እቃዎችን መወርወር
- ማን ማየት እንደሚችሉ እና ምን ማድረግ እንደሚችሉ መንገር
- ከእርስዎ ጋር ጾታዊ ግንኙነት እንዲፈጽሙ ማስገደድ
- ከጓደኞቻቸው እና ከቤተሰቦቻቸው ማግለል
- ገንዘብ ወይም ፋይናንስ እንዳያገኙ መከልከል

## ጾታዊ ጥቃት

ጾታዊ ጥቃት የተለያዩና ዘርፈ ብዙ የሆኑ የማይፈለጉ፣ በፈቃድ ያልተመሰረቱ፣ አሰቃቂ እና ጎጂ ወሲባዊ ባህሪያት ሲሆኑ፣ ይህም ወሲባዊ ትንኮሳ፣ መንካት፣ ማስገደድ፤ እንዲሁም አስገድዶ መድፈርን ጨምሮ ወሲባዊ ጥቃት ያጠቃልላል። የጾታ ጥቃት ወንጀል ነው።

## ድጋፍ፣ እርዳታ እና መረጃ ማግኘት

በትዳር ጓደኛዎ እና በቤተሰብዎ ዙሪያ ደህንነትዎ የተጠበቀ እንዲሆን የሚያስፈልጉትን ለውጦች ለማምጣት እገዛ እና ድጋፍ አለ።

ስለሚያውቁት ሰው ባህሪ የሚያሳስብዎት ከሆነ መረጃን ለመስጠት፣ ለማገዝ እና ድጋፍ ለመስጠት የሚረዱ አገልግሎቶችም አሉ።

# የድጋፍ አገልግሎቶች

ከድጋፍ አገልግሎት ጋር የሚያገናኝዎት አስተርጓሚ ከፈለጉ ወደ የትርጉም እና አስተርጓሚ አገልገሎት (TIS/ቲስ) በ 131 450 ይደውሉ።

ሁሉም ጥሪዎች ነፃ እና ምስጢራዊ ናቸው።

**በአደጋ ጊዜ፣ ሁሉጊዜ 000 ይደውሉ**

የወንዶች ከስልጣን በላይ (የማጣቀሻ) አገልግሎት
(Men's Referral Service)
**1300 766 491**
*24 ሰዓት ክፍት*
ነወየስልክ ምክር አገልግሎት፣ ላይቭ ቻት፣ መረጃ እና ወደ አከባቢ አገልግሎቶች መላክ። ይደዋዮ ማንነት በሚስጢር ይያዛል።
www.ntv.org.au

ወንዶች አዳዲስ ስልቶችን እንዲጠቀሙ የሚረዳ ፕሮግራም
(Men Engaging New Strategies Program)
**1300 364 277**
*ሰኞ እስከ ዓርብ፣ ከጠዋቱ 9 – ከሰዓት 5 ሰዓት*
የትዳር ጓደኛቸው ላይ በደል ለፈጸሙ ወንዶች በሪለሽንሺፕ አውስትራሊያ ታዝማኒያ
(Relationships Australia Tasmania)
የሚሰጥ ፕሮግራም።

ኢንጀንደር እኳሊቲ (Engender Equality)
**(03) 6278 9090**
*ሰኞ እስከ ዓርብ፣ ከጠዋቱ 9 – ከሰዓት 5ሰዓት*
የምክር እና የድጋፍ አገልግሎት ጥቃት ለሚያደርሱ፣ ሴቶችን ጨምሮ።
www.engenderequality.org.au

ሜንስላይን አወስትራሊያ (MensLine Australia)
**1300 789 978**
*24 ሰዓታት ክፍት ነው*
የስልክ እና የኦንላይን የምክር አገልግሎት ስነልቦናዊ የጤና ችግር ላለባቸው እና ግንኙነት ለሚያሳስባቸው ወንዶች።
www.mensline.org.au

በቤተሰብ ላይ የሚፈጸም እና ጾታዊ ጥቃት በጭራሽ ትክክል አይደለም።

እርስዎ ወይም የሚያውቁት ሰው በቤተሰብ ጥቃት ተጽእኖ ካጋጠምዎት፣ ወደ ደህንነት በቤት የቤተሰብ ዓመፅ ምላሽ እና የስልጣን በላይ መስመር (Safe at Home Family Violence Response and Referral Line) በ 1800 633 937 ይደውሉ።

እርስዎ ወይም የሚያውቁት ሰው በጾታዊ ጥቃት ተጽኖ ካጋጠምዎት፣ በክልላዊ ጾታዊ ጥቃት ቀውስ መስመር (Statewide Sexual Assault Crisis Line ) በ **1800 697 877** ይደውሉ። በአደጋ ጊዜ፣ ሁሉጊዜ በ **000 ይደውሉ።**

# ተጨማሪ መረጃ

ወደ አውስትራሊያ ለሚመጡ ሴቶችንና ወንዶችን የሚደግፍ ተጨማሪ መረጃ፣ የአውስትራሊያ የቤተሰብ ጥቃትን አስመልክቶ የወጡ ሕጎችን ጨምሮ ተጨማሪ መረጃ በ 46 ቋንቋዎች በዚህ ድረ-ገጽ **www.dss.gov.au/family-safety-pack ላይ ያገኛሉ።**